## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## <u>የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያዎች</u>

1. **በጁላይ 14 (ቅዳሜ)** አጠቃላይ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ስለሚኖረን የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ **<u>ጠዋት 10 ኤ.ም.</u>** ላይ በቤተክርስቲያን ተገናኝተን ጸልየን እንድንወጣ የአገልግሎቱ አስተባባሪዎች በማክበር ይጠይቃሉ።

2. በተለያየ ምክኒያት ወደኋላ የተመለሱ ወገኖችን ለመፈለግና ለመጎብኘት ሽማግሌዎች እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ስልሆን የምናውቀውና መጎብኘት አለበት የምትሉትን ስም ለወንድም ጌቱ እንድትሰጡ እናሳስባለን።

3. በቤተክርስቲያናችን በለዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ ያላችሁ አገልጋዮች በሙሉ ቀጥሎ በተገለጹት ቀናት ከእሁድ አምልኮ ፕሮግራም በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር ስብሰባ ስለሚኖረን በጊዜ ሰሌዳችሁ መሰረት እንድትገኙ በጌታ ፍቅር እናሳስባለን።

⇒ ጁላይ1 /2018 የቤት ለቤት ህብረት መሪዎች

⇒ ጁላይ8/2018 የልጆች አገልግሎት

⇒ ጁላይ15/2018 ኮሚኒኬሽን ሚዲያ

⇒ ጁላይ22/218 የእህቶች አገልግሎት

⇒ ጁን29/2018 ርህራዬ አገልግሎት



⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**

⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**

⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**

⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**

⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**

⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### <u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፥ በዝማሬም ለእርሱ እልል እንበል።"
(መዝ. 95:2)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**July 1, 2018** | **ሰኔ 24፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. ወንድም ረድኤቱ ካሳ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

ቃል ............. ወንድም ብርሃኑ አንበሴ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ።"

(መዝ. 50:23)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኀ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ግርማ ካሳ

### አምልኮ -- ትርጉም (አንድ)

የአምልኮን ትርጉም ከሚገልጹልን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ያደረገው ምልልስ አንዱ ነው። (ዮሐ. 4) በክፍሉ እንደምናነበው ጌታችን ከይሁዳ ወደ ገሊላ ለመሄድ ተነስቶ በሰማሪያ ማለፍ ግድ ሆነበት። (ቁ. 4) እንደ ዘመኑ ልማድና ባህል ከሆነ አንድ አይሁዳዊ በሰማሪያ አልፎ ወደ ገሊላ ከመሄድ ይልቅ በዙሪያ ጥምጥም መሄድን ይመርጣል። ምክንያቱም አይሁድና ሰማሪያዊያን የማይተባበሩ ስለነበር ነው። ጌታ ግን በሰማሪያ ማለፈን መረጠ። ይህ የጌታ አደራረግ በምሪት የሆነና የጠፋችን ነብስ ለማግኘት ባህሉ የደነገገውን ነውር በመስበር የተደረገ ነው።

ጌታ በሰማሪያ በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ውሃ ልትቀዳ በቀትር መጣች። በመሰረቱ በቀትር ውሃ አይቀዳም። ነገር ግን ሴቱቱ በማህበረሰቡ የተገለለች፣ የትዳር ችግር የነበረባት፣ በሕይወቷ እርካታ ያጣችና የተጠማች ስለነበረች ሌላ ምርጫ አልነበራትም። የሰፈርተኛውን አግቦና ስድብ ከመስማት ይልቅ ማንም በማያገኛት አደገኛ ሰዓት እንስራዋን ተሸክማ ውሃ ልትቀዳ መጣች። በዚያ ግን ያልጠበቀቻው ነገር ነው የገጠማት። ዛሬ የገጠማት ሰው የሚያገላት ሳይሆን ሊያናግራት የፈቀደና ውሃ አጠጪኝ ብሎ ጥማቷን ሊያረካ የመጣ ነው። ሴቲቱ ብዙ ጥያቄዎች ነበሯት። የጎሳ ግንኙነት ጥያቄ ነበራት። እንዴት አንድ አይሁዳዊ ወንድ ከሰማሪያዊት ሴት ጋር ይነጋገራል ትላለች። ደግሞም የታሪክ ትምክህት ነበራት። አባታችን ያዕቆብ የሰጠንን ውሃ ነው የምንጠጣው የምትል ነበረች። ደግሞሞ በሕይወት አለመርካት ችግር ነበራት። ብዙ ተጠምታለች፤ ብዙ ነገርም ሞክራለች ነገር ግን አልረካችም። በባሎች አልረካችም፣ በጎሳዋ አልረካችም፣ በታሪኳ አልረካችም፣ በአምልኮ ልምምዷም አልረካችም። ስለዚህ ጌታ የውስጧን ጥማት ገልጾ ሲያሳያት የአምልኮ ጥያቄዋን አነሳች። ምድንድን ነው ማምለክ? የት ነው የሚመለከው -- በተራራ ነው ወይንስ በኢየሩሳሌም፣ እንዴት ነው የሚመለከው? በማለት ጠየቀችው።

ጌታ ለዚህ ጥያቄ የሰጣት መልስ የአምልኮን ትርጉም ፍንትው አድርጎ ያሳየናል። ጌታ አምልኮ ለሚያደነው ጌታ መስገድ ነው አላት። (ቁ. 22) አምልኮ ለእግዚአብሔር በፍቅር መገዛት ነው። አምልኮ እግዚአብሔርን መውደድ ነው። እውነተኛ አምልኮ በሕወታችን ለእግዚአብሔር የምሰጠው ስፍራ ነው። እግዚአብሔር በሕይወታችን አንደኛ (ቀዳሚ) ከሆነ እርሱን እያመለክን ነው። ነገር ግን በሕይወታን ከእግዚአብሔር ይልቅ ስፍራ የምንሰጠው ሌላ ነገር ካለ ጣኦትን እያመለክን ነው ማለት ነው። አምልኮ በልባችን ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ስፍራ ነው። አምልኮ እግዚአብሔር ከምፍራትና ከመውደድ የተነሳ ለእርሱ መቀደስ ነው። አምልኮ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ዋጋ ነው። የአምልኮ የእንግሊዘኛ አቻ ቃል "worship" የመጣው "worth ship" ከሚለው ኃረግ ነው። ይህም አምልኮ ማለት በሕይወታችን ለእግዚአብሔር የምሰጠውን ዋጋ መግለጽ እንደሆነ ያሳየናል።

ወገኖቼ፡- ኢያሱ እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን እንዳለ እኛና ቤታችንም በሕይወታችን እግዚአብሔርን በማስቀደምና የሚገባውን ስፍራ በመስጠት እርሱን የምናመልክ እንድንሆን የጌታ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሆን። አሜን!